# የግምገማ ፍኖተ–ካርታ

ዕድሜአቸው ከ3 - 21 ዓመት የሆኑ ልጆች ላሏቸው ቤተሰቦች

– ለተጨማሪ መረጃዎች እነዚህ አይከኖች (የፋይል ወይም የፕሮግራም ምልክቶች) ላይ ጠቅ ያድርጉ።

**1 ስለልጅዎ ትምህርት የሚያሳስቡዎ ጉዳዮች አሉዎት**

የልጅዎን መምህር ወይም የዲስትሪክቱን የልዩ ፍላጎት ትምህርት ዳይሬክተር ያነጋግሩ።

**2 ጣልቃ-ገብ እገዛዎች (Interventions) እና ግምገማ እንዲካሄድ የመፈለግ ጥያቄ በንፅፅር**

የት/ቤት ዲስትሪክቶች የሚቸገሩ ተማሪዎችን በሙሉ ለመርዳት የመማር-ማስተማር ሁኔታን እንዲያስተካክሉ በሕግ ይገደዳሉ። ግምገማ እንዲካሄድ የመፈለግ ጥያቄዎች ከጣልቃ-ገብ እገዛዎች (Interventions) ጋር አንድ ዓይነት አይደሉም።

የወላጅ መብቶች

**3 ግምገማ እንዲካሄድ የመፈለግ ጥያቄ**

የልዩ ትምህርት ፍላጎት ግምገማን በማንኛውም ጊዜ መጠየቅ ይችላሉ።

30 ቀኖች

ዲስትሪክቱ የአካል ጉዳተኝነት መኖርን አልጠረጠረም

በአጠቃላይ ትምህርት(general education) ይቀጥል ...

ወይም በOhio Department of Education (የኦሃዮ የትምህርት ዲፓርትመንት) በኩል የቅሬታ አቤቱታ መመልከቻ ሂደትን ይከተሉ"በ ዚህ ሊንክ (አገናኝ)።

PR-01

**4 የአካል ጉዳተኝነት መኖሩ ተጠርጥሯል ግምገማ እንዲካሄድ ስምምነት**

PR-05

60 ቀኖች

**5 የግምገማ ሂደት**

በሁሉም አሳሳቢ ዘርፎች ዙሪያ የሚደረግን ግምገማ ለማቀድ ወላጆችን ጨምሮ ብቃት ያላቸው ግለሰቦችን የያዘ ቡድን ይሰበሰባል።

PreK

ዕድሜው ለት/ቤ የደረሰ

**6 የመጀመሪያ ግምገማ አድራጊ ሪፖርት ተጠናቋል ቡድን**

ወላጆችን ጨምሮ ቡድኑ ውጤቱን ድጋሚ ለማየት (ለመከለስ) ይሰበሰባል።

PR-02

ETR

**7 የብቁነት ውሳኔ**

30 ቀኖች

የብቁነት ቡድን ልጁ ብቁ አይደለም ብሎ ይወስናል

በአጠቃላይ ትምህርት (general education) ይቀጥል

**8 የመጀመሪያ ግለሰባዊ የትምህርት እቅድ (IEP) ተዘጋጅቷል**

ወላጆችን ጨምሮ ቡድኑ ልጁ ብቁ ነው ብለው ከወሰኑ ግለሰባዊ የትምህርት እቅድ (IEP) ይዘጋጃል

ግለሰባዊ የትምህርት እቅድ (IEP)

**9 የመጀመሪያ ግለሰባዊ የትምህርት እቅድ (IEP) ተተግብሯል**

ዲስትሪክቱ በተማሪው ግለሰባዊ የትምህርት እቅድ (IEP) የተካተቱ አገልግሎቶችን እንዲሰጥ ሕግ ያስገድደዋል።

Ohio | Department of Education

# የግምገማ ፍኖተ–ካርታ

ዕድሜአቸው ከ3 - 21 ዓመት የሆኑ ልጆች ላሏቸው ቤተሰቦች

## 1. ስለልጅዎ ትምህርት የሚያሳስቡዎ ጉዳዮች አሉዎት

- ስለልጅዎ ትምህርት፣ እድገት ወይም እንቅስቃሴ (ነገሮችን መሥራት ስለመቻል/አለመቻል) የሚያሳስቡጉዳዮች ካሉዎት የልጅዎን መምህር ያነጋግሩ። የዲስትሪክቱን የልዩ ፍላጎት ትምህርት ዳይሬክተርም ለማነጋገር ይችላሉ። ይህ ሰው ማን እንደሆነ የማያውቁ ከሆኑ ወደ ቦርዱ ጽ/ቤት በመደወል ወይም ኢሜል በማድረግ ስም እና የማግኛ መረጃን እንዲሰጥዎ ይጠይቁ። የልጅዎ ት/ቤት ር/መምህርንም ለማነጋገር ይችላሉ።
- ለቅድመ መደበኛ ት/ቤት  (ከ3-5 ዓመት ዕድሜ ውስጥ ላሉ):- ልጅዎ በእንቅስቃሴ፣ በእድገት እና/ወይም በትምህርት ዝግጁነት መስኮች ዝግመቶች እንዳሉበት ለማየት የመጀመሪያው እርምጃ እርስዎ ወላጁ በሚኖሩበት የሚገኘውን የት/ቤት ዲስትሪክት ማነጋገር ነው። የአብዛኞቹ የት/ቤት ዲስትሪክቶች የአድራሻ መረጃ በዲስትሪክቱ ዌብሳይት (ድረ-ገጽ) ላይ መገኘት ይችላል።

## 2. ጣልቃ–ገብ እገዛዎች (Interventions) እና ግምገማ እንዲካሄድ የመፈለግ ጥያቄ በንፅፅር

- **ጣልቃ–ገብ እገዛ (Intervention):-** የት/ቤት ዲስትሪክቶች የመማር ማስተማር ሂደታቸው ሁሉንም ተማሪዎች ሊያግዝ በሚችል መልኩ እንዲያካሂዱ ይገደዳሉ። የመማር ማስተማር ሂደቱን የሚቸገሩ ተማሪዎችን ሊያግዝ በሚችል መልኩ የማስተካከል ስልቶች (ኢንተርቬንሽንስ) እገዛዎች የሚባሉ ሲሆኑ ለሁሉም ተማሪዎች ናቸው (ለልዩ ፍላጎት ተማሪዎች ብቻ አይደሉም)።
- **ግምገማ እንዲካሄድ የመፈለግ ጥያቄ:-** ለልዩ ፍላጎት ትምህርት ግምገማ እንዲካሄድ የመፈለግ ጥያቄን ማቅረብ ከጣልቅ-ገብ እገዛዎች (Interventions) ጋር አንድ አይደለም። ጣልቅ-ገብ እገዛዎች (Interventions) ከግምገማው በፊት ወይም ግምገማው በሚደረግበት ወቅት መሰጠት አለባቸው። አንድ የት/ቤት ዲስትሪክት ግምገማን ለማዘግየት ጣልቅ-ገብ እገዛዎችን (Interventions) መጠቀም አይችልም። ጣልቅ-ገብ እገዛዎች (Interventions) ተሰጥተው ካልሆነ ከግምገማው ጋር በተመሳሳይ ጊዜ መሰጠት አለባቸው።

ወደ ፍኖተ–ካርታ ይመለሱ

# የግምገማ ፍኖተ–ካርታ

ዕድሜአቸው ከ3 - 21 ዓመት የሆኑ ልጆች ላሏቸው ቤተሰቦች

## 3. ግምገማ እንዲካሄድ የመፈለግ ጥያቄ

- ልጅዎ ጉዳት ወይም ዝግመት አለበት ብለው ከጠረጠሩ ለልዩ ፍላጎት ትምህርት ግምገማ እንዲደረግለት መጠየቅ ይችላሉ። ጥያቄው በጽሑፍ መሆን አይኖርበትም፤ ነገር ግን ለራስዎ መረጃ እንዲሆን የጠየቁበትን ቀን መመዝገብ ጥሩ ነው።
- ለቅድመ መደበኛ ት/ቤት እንደ ወላጅ በት/ቤት ዲስትሪክዎ የልዩ ፍላጎት ትምህርት ባለሙያ የሆነ ሠራተኛን በሚያነጋግሩበት ጊዜ ልጅዎ በቅድመ መደበኛ ት/ቤት የልዩ ፍላጎት ትምህርት አገልግሎቶችን ማግኘት ይችል እንደሆነ እና የትኞቹ ፕሮግራሞች ግላዊ ፍላጎቱን የሚስማሙ እንደሆነ በመጠየቅ ግምገማ እንዲካሄድ የመፈለግ ጥያቄዎን መጀመር ይችላሉ።
- ዲስትሪክቱ ጥያቄዎ ከደረሰው ዕለት አንስቶ በ30 የካሌንደር ቀኖች ውስጥ ለጥያቄዎ ምላሽ ይሰጣል። ዲስትሪክቱ ምንም ዓይነት ጉዳት ወይም ዝግመት እንደማይጠረጥር ወይም ግምገማውን ለማካሄድ የእርስዎን ስምምነት ለማግኘት አስቀድሞ (PR-01 የተባለውን) የጽሑፍ ማስታወሻ (ወደ PR-01 ቅጽ ሊንክ (አገናኝ)) ይልክልዎታል። ዲስትሪክቱ የልዩ ትምህርት ሂደት ማስጠበቂያዎች ማስታወሻ ቅጅን ይልክልዎታል፤ማስታወሻውም "A Guide to Parent Rights in Special Education (በልዩ ፍላጎት ትምህርት ውስጥ የወላጆች መብቶች መመሪያ)" የሚል ነው።
- አንድ ዲስትሪክት ጣልቃ-ገብ እገዛዎችን (interventions) ለመስጠት ሲል ግምገማን ማዘግየት አይፈቀድለትም። ዲስትሪክቱ ከግምገማው በፊት ጣልቃ-ገብ እገዛዎችን (interventions) ገና ያልሰጠ ከሆነ ዲስትሪክቱ እገዛዎቹን ከግምገማው ጋር በተመሳሳይ ጊዜ መስጠት አለበት።
- ዲስትሪክቱ ጉዳት/ዝግመት ካልጠረጠረ ልጅዎ በአጠቃላይ ትምህርቱ (general education) ይቀጥላል። በዲስትሪክቱ ውሳኔ ካልተስማሙ በዚህ ሊንክ (አገናኝ) በ Ohio Department of Education (ኦሃዮ የትምህርት ዲፓርትመንት) በኩል የቅሬታ አቤቱታ መመልከቻን ማስገባት ይችላሉ።

## 4. ግምገማ እንዲካሄድ ስምምነት

- ዲስትሪክቱ ጉዳት/ዝግመት አለ ብሎ ከጠረጠረ በጽሑፍ የተገለጸ ስምምነትዎን ይጠይቅዎታል (የስምምነት ቅጹ PR-05: የወላጅ ስምምነት ለግምገማ ይባላል) (ወደ ስምምነት ቅጹ የሚወስድዎ ሊንክ (አገናኝ))። ስምምነትዎን ከሰጡበት ቀን አንስቶ ዲስትሪክቱ ግምገማውን አድርጎ ለማጠናቀቅ 60 የካሌንደር ቀኖች ይኖሩታል።
- ለቅድመ መደበኛ ት/ቤት፡- ከ3-5 ዓመት የሆነው ልጅዎ የቅድመ መደበኛ ት/ቤት ፕሮግራም ተከታትሎ የማያውቅ ከሆነ ወይም ልጅዎ ከIDEA Part C (ቅድመ መደበኛ እገዛ) ወደ Part B (የልዩ ፍላጎት ትምህርት) ያልተሸጋገረ ከሆነ ት/ቤቱ ለልጅዎ እገዛዎችን ለመስጠት እድሉ ያልነበረው ሊሆን እንደሚችል ልብ ማለት በጣም አስፈላጊ ነው። ለቅድመ መደበኛ ልጆች ጣልቃ-ገብ እገዛዎች (interventions) አስገዳጅ የሚሆኑት ልጁ ቀደም ሲል በIDEA ውስጥ በPart C እና/ወይም Part B አገልግሎቶችን ያገኝ ከነበረ ወይም በውሱን የትምህርት ጉዳት/ዝግመት ምድብ ውስጥ ለተለዩ ጉዳቶች/ዝግመቶች በመገምገም ላይ ያለ ከሆነ ብቻ ጣልቃ-ገብ እገዛዎች (interventions) አስገዳጅ ይሆናሉ። ከሪፈራል አስቀድሞ ጣልቃ-ገብ እገዛዎች (interventions) ያልተሰጡ ከሆኑ የት/ቤት ዲስትሪክቱ በአንድ ወይም ከአንድ በላይ በሆኑ በሚከተሉት የእድገት መስኮች ውስጥ ጠንካራ ዝግመቶች ለገጠመው ለማንኛውም የቅድመ መደበኛ ት/ቤት ልጅ ችግሩን ለመፍታት ሙሉ የግላዊ ግምገማ በሚደረግለት ጊዜ ማለትም በስልሳዎቹ ቀናት የጊዜ ማዕቀፍ ውስጥ ተገቢ የሆኑትን ጣልቃ-ገብ እገዛዎችን (interventions) ሊተገብር ይችላል። የመላመድ ባሕሪ፣ ግንዛቤ/እውቀት፣ ተግባቦት፣ መስማት፣ ማየት፣ የስሜት/የአካል ተግባራት፣ ማኅበራዊ/ስሜታዊ ተግባሮች እና/ወይም የባሕሪ ተግባራት። ልጁ ለልዩ ፍላጎት ትምህርት አገልግሎቶች ብቁ መሆን አለመሆኑን ለመወሰን የት/ቤት ዲስትሪክቱ እነዚህን ጣልቃ-ገብ እገዛዎችን (interventions) ግምገማውን ባላስፈላጊ ሁኔታ ለማዘግየት መጠቀም አይችልም።

ወደ ፍኖተ–ካርታ ይመለሱ

# የግምገማ ፍኖተ–ካርታ

ዕድሜአቸው ከ3 - 21 ዓመት የሆኑ ልጆች ላሏቸው ቤተሰቦች

## 5. የግምገማ ሂደት

- ዲስትሪክቱ ልጁ ግምገማ ይደረግለታል ብሎ ከወሰነ እርስዎን እንደ ወላጅ ጨምሮ ብቃት ያላቸው ግለሰቦችን የያዘ ቡድን መገምገም በሚያስፈልጋቸው የሚጠረጠሩ የጉዳት/ዝግመት ምድቦች እና መስኮች ላይ ውይይት ያደርጋል። ይህ ሁሉም ለቅድመ መደበኛ ት/ቤት እና ለመደበኛ ት/ቤት ልጆች የተለያየዩ ቅጾች ባሉት በገምጋሚው ቡድን ሪፖርት (ETR) እቅድ ቅጽ ላይ መሠነድ አለበት። (የቅድመ መደበኛ ት/ቤት ቅጽ ሊንክ (አገናኝ)) (የመደበኛ ት/ቤት ቅጽ ሊንክ (አገናኝ))
- ልጅዎን የትኞቹ ድጋፎች እጅግ የበለጠ ሊረዱት እንደሚችሉ ለመወሰን ሁሉም የፍላጎት ዘርፎች መገምገም ያስፈልጋቸዋል።
- ዲስትሪክቱ ለመገምገም ያቀደውን ዘርፍ ብቻ እንጅ የሚጠቀማቸውን ዝርዝር የግምገማ ዓይነቶች ስም መጥቀስ አይኖርበትም። ለቅድመ መደበኛ ት/ቤት:- እያንዳንዱ የእድገት መስክ መገምገም አለበት።
- የእቅድ ስብሰባው አንዳች ግምገማ ከመካሄዱ በፊት መካሄድ አለበት። በዚህ ቡድን ውስጥ እርስዎ እንደ ወላጅ የሚካሄዱ ምዘናዎችን በተመለከተ በሚደረገው ውሳኔ ለማገዝ ንቁ አባል ይሆናሉ።
- ለቅድመ መደበኛ ት/ቤት:- እያንዳንዱ የእድገት መስክ ከ 5ቱ የምዘና ዘዴዎች/የመረጃ ምንጮች ቢያንስ አንዱን በመጠቀም መመዘን አለበት። እንዲሁም እያንዳንዱ የምዘና ዘዴ/የመረጃ ምንጭ ቢያንስ አንድ ጊዜ ጥቅም ላይ መዋል አለበት። ሁሉንም የልጁን የልዩ ፍላጎት ትምህርት እና የሚያስፈልጉ ተያያዥ አገልግሎቶችን ለመለየትና አገልግሎቶቹ ልጁ ከተለየበት የጉዳት/ዝግመት ምድብ ጋር የተገናኙ ሆኑም አልሆኑም ግምገማው በበቂ ሁኔታ ሁሉን-አቀፍ መሆን እንዳለበት ያስታውሱ።

## 6. የመጀመሪያ የግምገማ ቡድን ሪፖርት ተጠናቅቋል

- የግምገማውን የጥናት መረጃ እና የተደረገውን የእያንዳንዱን ግምገማ ማጠቃለያ ድጋሚ ለማየት/ለመከለስ እንደ ወላጅውነትዎ (PR-02 የተባለ) የወላጅ የግብዣ መጥሪያ ይደርስዎታል። የሚላከው PR-02 ዲስትሪክቱ ለስብሰባው ማንን እንደሚያመጣ መግለጽ አለበት። እርስዎም እንደወላጅ የፈለጉትን ሰው ወደ ስብሰባው ይዘው መምጣት ይችላሉ።
- የባለሙያዎች ቡድን እና ወላጅ በጋራ የግምገማውን ውጤቶች ከልሰው ልጁ ጉዳት/ዝግመት ያለበት መሆን አለመሆኑን ይወስናሉ። (የ ETR ቅጽ ሊንክ (አገናኝ))

ወደ ፍኖተ–ካርታ ይመለሱ

# የግምገማ ፍኖተ–ካርታ

ዕድሜአቸው ከ3 - 21 ዓመት የሆኑ ልጆች ላሏቸው ቤተሰቦች

## 7. የብቁነት ውሳኔ

- ቡድኑ እንደወላጅ እርስዎን ጨምሮ ልጁ ለልዩ ፍላጎት ትምህርት አገልግሎቶች ብቁ ሆኖ ካገኘው የብቁነት ምድቡን የሚወስን/የሚለይ ይሆናል። ቡድኑ ልጅዎን ብቁ ሆኖ ካላገኘው ልጅዎ በአጠቃላይ ትምህርት (general education) ሥርዓተ ትምህርት ብቻ የሚቀጥል ይሆናል። ወላጁን ጨምሮ ማንኛውም የቡድን አባል በቡድኑ ውሳኔ ካልተስማማ በውሳኔው እንዳልተስማማ መግለጫ ሊያቀርብ/ሊያስገባ ይችላል። ልጅዎ ብቁ ሆኖ ካልተገኘ ገለልተኛ የሆነ ትምህርታዊ ግምገማ እንዲደረግ መጠየቅ ይችላሉ። IEE ወላጅ በዲስትሪክቱ የማይቀጠር የውጭ ባለሙያ አግኝቶ የግል ትምህርታዊ ግምገማ እንዲያካሂድ የሚያስችለው ዕድል ነው።
- ለቅድመ መደበኛ ት/ቤት፡- ልጅዎ ብቁ ሆኖ ካልተገኘ እና በአሁኑ ሰዓት በቅድመ መደበኛ ት/ቤት ፕሮግራም ውስጥ ተመዝግቦ የሚገኝ ከሆነ ዲስትሪክቱ ሊገኙ የሚችሉ አማራጭ የአካባቢ እና/ወይም በት/ቤት ዲስትሪክቱ የሚመሩ ፕሮግራሞች ዝርዝርን ሊሰጥ ይችላል።

## 8. የመጀመሪያ ግለሰባዊ የትምህርት እቅድ (IEP) ተዘጋጅቷል

- እንደወላጅ እርስዎን ጨምሮ ቡድኑ ልጅዎ ለልዩ ፍላጎት ትምህርት ብቁ ነው ብሎ ከወሰነ ዲስትሪክቱ ለልጁ የግለሰባዊ የትምህርት እቅድን (IEP) ለማዘጋጀት 30 ቀኖች ይኖሩታል። (የ ETR ቅጽ ሊንክ (አገናኝ))
- ግለሰባዊ የትምህርት እቅዱ (IEP) በልጅዎ ገምጋሚ ቡድን ሪፖርት (ETR) ውስጥ የተለዩትን ግለሰባዊ ፍላጎቶች ሊለኩ ከሚችሉ ግቦች እና ዓላማዎች እና ከለውጥ/መሻሻል መለኪያ ጋር ለማሳካት በተለየ ሁኔታ የተነደፈ ትምህርትን መያዝ አለበት።
- የIEP (የግለሰባዊ የትምህርት እቅድ) ቡድኑ እንደወላጅ እርስዎን፣ አንድ መደበኛ የልጁን አስተማሪ (ልጁ አስተማሪ ያለው ከሆነ)፣ ቢያንስ አንድ የልዩ ፍላጎት ትምህርት መምህር፣ አንድ የዲስትሪክት ተወካይ፣ የግምገማ ውጤቶችን የሚተነትን አንድ ሰው እና እርስዎ ወይም ዲስትሪክቱ ስለልጁ እውቀት ወይም ፍላጎት አለው ብላችሁ ያመናችሁበት ሰውን ያካትታል።
- ለቅድመ መደበኛ መካተት ያለባቸው የIEP (የግለሰባዊ የትምህርት እቅድ) ቡድን አባላት የሚከተሉት ናቸው፡- ወላጅ፣ የአጠቃላይ ትምህርት መምህር፣ የልዩ ፍላጎት ትምህርት መምህር/አገልግሎት ሰጪ እና የዲስትሪክት ተወካይ።
- ለመጀመሪያ የIEP (የግለሰባዊ የትምህርት እቅድ) አገልግሎቶች እርስዎ እንደ ወላጅ ስምምነትዎን መስጠት አለብዎ። ስምምነትዎን ካልሰጡ ልጅዎ የIEP አገልግሎቶችን የሚያገኝ አይሆንም።
- የእርስዎ ስምምነት ለመጀመሪያ የግለሰባዊ የትምህርት እቅድ (IEP) (ወይም ማንኛውም የትምህርታዊ ምደባ ለውጥ) ብቻ ግዴታ ተፈላጊ ቢሆንም የት/ቤት ዲስትሪክቶች በሁሉም የግለሰባዊ የትምህርት እቅድ (IEP) ስብሰባዎች እንዲገኙ እና እንዲሳተፉ እንዲጋብዙዎ ይገደዳሉ። ለልጅዎ የግለሰባዊ የትምህርት እቅድ (IEP) የሰጡትን ስምምነት በማንኛውም ጊዜ የማንሳት ወይም የመሻር መብት አለዎ።

ወደ ፍኖተ–ካርታ ይመለሱ

# የግምገማ ፍኖተ–ካርታ

ዕድሜአቸው ከ3 - 21 ዓመት የሆኑ ልጆች ላሏቸው ቤተሰቦች

## 9. የመጀመሪያ ግለሰባዊ የትምህርት እቅድ (IEP) ተተግብሯል

- ዲስትሪክቱ በልጅዎ ግለሰባዊ የትምህርት እቅድ (IEP) የተካተቱ አገልግሎቶችን መስጠት ይኖርበታል።
- እያንዳንዱ የት/ቤት ዲስትሪክት ለእያንዳንዱ ጉዳት/ዝግመት ላለበት ልጅ ነፃ እና አግባብ የሆነ የሕዝብ ትምህርት (FAPE) እጅግ በጣም በዝቅተኛ ሁኔታ ገዳቢ በሆነ አካባቢ/ሁኔታ ውስጥ (LRE) መስጠቱን ማረጋገጥ አለበት። ለቅድመ መደበኛ ት/ቤት፣ ይህ ዲስትሪክቱ የራሱን አጠቃላይ የቅድመ መደበኛ ት/ቤት ፕሮግራሞችን ቢያስተዳድርም ሆነ ለትምህርታዊ ኤጀንሲዎች ኮንትራት ቢሰጥም በማንኛውም ሁኔታ የሚሠራ ነው።

ወደ ፍኖተ–ካርታ ይመለሱ